# የኢትዮጵያ የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ ስርዓት መመሪያ

**የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚንስቴር**

**ነሀሴ፣ 2011ዓ.ም**

## መውጫ


**መግቢያ** ........ 3

**ክፍል አንድ** ........ 4

ጠቅላላ ሁኔታዎች ........ 4

1. አውጪው ባለስልጣን ........ 4
2. አጭር ርዕስ ........ 4
3. የዚህ መመሪያ ዓላማ ........ 4
4 ትርጓሜ ........ 4
5. የተፈጻሚት ወሰን ........ 6

**ክፍል ሁለት** ........ 6

መሰረታዊ የአለባበስ ስርዓት መርሆች ........ 6

2.1 ሙያዊ ገጽታ፤ ንጽህናና አለባበስ ........ 6
2.2 ጌጣጌጥና መዋቢያ ........ 7
2.3 የግል ኤሌክትሮኒክስ መጠቀሚያ ........ 7
2.4 የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የደንብ ልብስ አይነት እና ቀለም ........ 8
2.5 የደንብ ልብስ ይዘት ........ 8

**ክፍል ሶስት** ........ 9

**3.1 የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት** ........ **9**

3.1.1. የጤና ሚኒስቴር ተግባር እና ሀላፊነት ........ 9

3.1.2. የክልል ጤና ቢሮ ተግባር እና ሀላፊነት ........ 9

3.1.3. የጤና ተቋማት ማኔጅመንት ተግባር እና ሀላፊነት ........ 10

3.1.4. የጤና ባለሙያዎች አለባበስ ስርዓት ኮሚቴ መመስረት እና ተግባር እና ሀላፊነት ........ 10

3.1.5. የባለሙያዎች እና ተማሪዎች ተግባር እና ሀላፊነት ........ 11

**ክፍል አራት** ........ **11**

**ልዮ ልዮ ድንጋጌዎች** ........ **11**

4.1 የመተባበር ግዴታ ........ 11
4.12 መመሪያው የሚሻሻልበት አግባብ ........ 11
4.13 የተሻሩ እና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች እና አሰራሮች ........ 12
4.14 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 12

# መግቢያ

የጤና ሚኒስቴር በጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የተለያዩ የሪፎርም ስራዎችን እየተገበረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አግባብ ያለው የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ ስርዓት በጤና ተቋማት ላይ መዘርጋት አንዱ እስታንዳርድ እና ዋነኛው ሁኖ በመገኘቱ፡-

በጤናው ሴክተር የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተቀመጡ አጀንዳዎች አንዱ የሆነው ሩህሩህ ተገልጋይን አክባሪ ተንከባካቢ እና ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሱ ጤና ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚደረገውን ንቅናቄ ለማጠናከር፡-

የጤና ባለሙያዎችን የአለባበስ ስርዓት በጤና ተቋማት ውስጥ ወጥ ለማድረግ፣ተገልጋዩ ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጠውን ባለሙያ ማንነት በቀላሉ እንዲያውቅና የጤና አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ግልፅና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ለመዘርጋት እንዲሁም ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል፡-

በጤና ተቋማት የሚያገለግሉ ባለሙያዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከተላለፊ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጣር ንፅህናውን የጠበቀና ስርዓት ያለው ሙያዊ አለባበስ መፍጠር እንዲያስችል ፡-

የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ ስርዓት የባለሙያውን ሙያዊ ገፅታ በመገንባትና ሙያዊ ክብር እንዲሰማው ከማድረጉም ባሻገር ተገልጋዩ ማሕበረሰብ በሚገለገልበት ተቋም እና በሚያገለግለው ባለሙያ አመኔታ ለማሳደር ፡-

የኢፌድሪ የጤና ሚኒስቴር ይህንን የኢትዮጵያ የጤና ባለሞያዎች የአለባበስ ስርዓት መመርያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ሁኔታዎች

## 1. አውጪው ባለስልጣን

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ሚኒስቴር የጤና ተቋማት ሀገር አቀፍ የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ ስርዓት ወጥ በሆነ መልኩ ለመዘርጋት በአስፈፃሚ አካላት ስልጣን እና ተግባር አወሳሰን **አዋጅ ቁጥር** 1097/2011 **አንቀፅ** 27(1) **እና አዋጅ ቁጥር** 661/2009 **አንቀፅ** 55(1) መሰረት ይህ መመሪያው አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የጤና ሚኒስቴር የጤና ባለሞያዎች የስራ ላይ የአለባበስ ስርዓት መመሪያ ቁጥር ---- /2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የዚህ መመሪያ ዓላማ

1. ጤና ባለሙያውን እና ተገልጋዩን ማህበረሰብ ከተላላፊ በሽታዎች እና ጉዳቶች መከላከል
2. ጤና ባለሙያው በሙያው እንዲኮራ እና ሙያዊ ፍቅር እንዲያጎለብት ማገዝ
3. ተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚያገለግሉትን ጤና ባለሙያዎች በቀላሉ መለየት እና መግባባት እንዲችል ማድረግ
4. ተገልጋዮ ማህበረሰብ በጤና ተቋማቱ እና አገልግሎቱን በሚሰጠው ባለሙያ እምነት እንዲኖረው ማስቻል
5. በጤና ተቋማትና በባለሙያዎች ዘንድ ተጠያቂነት እና ግልፀኝነት መፍጠር

## 4 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

4.1. “**ጤና ተቋም**” ማለት፡- በሀገሪቱ ውስጥ ለተገልጋዮ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ እና ቀጥተኛ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ሆስፒታሎችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣የህክምና ማእከሎችን እና ክሊኒኮችን ያጠቃልላል፡፡

4.2. **"ጤና ባለሙያ"** ማለት፡ በጤና ሳይንስ ትምህርት በፒኤቺዲ/በማስተርስ/በህክምና ስፔሻሊያዜሽን፣በሜዲካል ዶክትሬት ዲግሪ/በዲግሪ/በዲፕሎማ እና በቲቪቲ የተመረቀ ሁኖ አግባብ ያለው የሙያ ፈቃድ ያለው እና ለተገልጋዩ ማህበረሰብ በጤና ተቋማት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት የሚሳተፈውን ባለሙያ ሁሉ ያካትታል፡፡

4.3. **"የጤና ባለሙያ የአለባበስ ስርአት"፡-**ማለት በጤና ተቋም ውስጥ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች በስራ ቦታቸው የደንብ ልብስ፣ የጸጉር እና የጥፍር አያያዝ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ እቃዎች፣የግል ኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች አጠቃቀም እና የግል ንጽህናን የሚያጠቃልል ነው፡፡

4.4. **ሙሉ የደንብ ልብስ፡** ማለት ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ስራውን ሲያከናውን የሚለብሰው ደረጃውን የጠበቀ የልብስ አይነት ነው፡፡ ይህም ሲባል

- ወንድ/ሴት የጤና ባለሙያ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የተለያዮ ቀለማትን ያገናዘበ ከላይ አላባሽ አንገቱ ዋይ (y) ወይም ቪ(v) ቅርፅ የሆነ እጅጌው ከክርን በላይ፣ ሱሪ ወገቡ ማሰሪያ ያለዉ እና ዶክተር ጫማ ሲሆን ቀሚስ ወይም ጉርድ ለሚለብሱ ተመሳሳይ y ወይም v ቅርፅ ሆኖ ከጉልበት በላይ ያላጠረ መሆን አለበት፡፡

4.5. **ሙያዊ ገጽታ፡** የማህበረሰቡን እሴት ያከበረ ፣ ሙያውን የሚገልፅ ፣ በተገልጋዮች በቀላሉ የሚለይና የበሽታ ስርጭትን መከላካል የሚያስችል የአለባበስና የባህሪ ሁኔታ ነው ፡፡

4.6. **የግል ኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች** ማለት ተቋሙ ለጤና ባለሙያው ለአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ብሎ ከሰጠው ውጭ የሆነ የግል የኤሌክትሮኒክ እቃዎች በጠቅላላ ሲሆን ሞባይል ስልክ፣ላፕቶፕ፣ ታብሌት ኮምፒውተር፣በጆሮ ላይ የሚደረጉ የሙዚቃ ማዳመጫን ያጠቃልላል ፡፡

4.7. **የጤና ሳይንስ ተማሪዎች** ማለት በጤና ሳይንስ ትምህርት በተለያዮ የትምህርት መስኮች በፒኤቺዲ ፣ በማስተርስ ዲግሪ ፣ በህክምና ስፔሻሊያዜሽን፣ በሜዲካል ዶክትሬት ዲግሪ፣ በዲግሪ ፣ በዲፕሎማ እና በቲቪቲ የሚማሩ ሁነው ለ ተግባራዊ ልምምድ በየጤና ተቋማት ውስጥ የተመደቡ ናቸው፡፡

4.8. **ጠቅላላ የጤና አገልግሎት መስጫ ክፍል፡** የጤና ባለሙያ አገልግሎት የሚሰጡበት ከቀዶ ጥገና፣ፅኑ ሁሙማን ፣ ማዋለጃ እና ድንገተኛ ክፍል ውጪ ያሉ የጤና አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

4.9. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው በሙሉ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

በኢትዮጵያ በሚገኙ በሁሉም የመንግስት፣ የግል እና የግብረሰናይ የጤና ተቋማት ውስጥ በሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች እና ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## መሰረታዊ የአለባበስ ስርዓት መርሆች

### 2.1 ሙያዊ ገጽታ፤ ንጽህናና አለባበስ

2.1.1. የጤና ባለሙያ አለባበስ ሙያዊ ገፅታን የተላበሰ ፣ ንፁህና በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት መሆን አለበት፡፡

2.1.2. ሁሉም ባለሙያ በስራ ገበታው ላይ በሚገኝበት በማንኛውም ጊዜ ማንነቱና ሙያውን በሚገባ የሚገልፅ ባጅ ማደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.3. የሚዘጋጀዉ ባጅ የተቋሙን ስም፣የባለሙያዉን ሙሉ ስም፣ፎቶ፣የሙያ መጠሪያዉን/የስራ ድርሻ/ ያካተተ መሆን አለበት፤

2.1.4. ማንኛዉም የጤና ባለሙያ በስራ ቦታ ላይ ከስራ ኮፍያና ከሃይማኖት መለዮ በስተቀር መጠቀም የማይፈቀድ ሲሆን ፤ የእምነት የጸጉር መሸፈኛ የፊት ገፅታን ለመለየት የሚያስቸግር መሆን የለበትም፡፡

2.1.5. በስራ ገበታ ላይ የምንጠቀመው ጫማ ምቹ ፣ ንጹህ ፣ ክፍት ያልሆነ ፣ ድምፅ የማይፈጥር ፣ የጫማውም የተረከዝ መጠን ዝቅተኛ የሆነና የስራ ቅልጥፍናን የማያደናቅፍ መሆን አለበት፡፡

2.1.6. በመመሪያው የተቀመጠውን ዩኒፎርም ለመልበስ ችግር የሚገጥመዉ ባለሙያ በተለይም ከአካል ጉዳት ጋር እና እርግዝና ጋር ተያያዥ የሆነ ሁኔታ ሲኖር በጤና ተቋሙ አመራር ሊስተናገድ ይችላል ፡፡

2.1.7. የደንብ ልብሱን ከተፈቀደው የስራ ቦታ በስተቀር ለብሶ መንቀሳቀስ አይፈቀድም፡፡

2.1.8. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የደንብ ልብሱን ከተቀመጠው መስፈርት ወጪ አድርጎ ማሻሻል ወይም መለወጥ አይችልም፡፡

2.1.9. የደረት መለያ ባጅ የጤና ተቋሙ በሚገኝበት አካባቢ  የስራ ቋንቋ እና በፌድራል ስራ ቋንቋ መፃፍ ይኖርበታል።

2.1.10. ሁሉም ጤና ባለሙያ ከአየር ንብረቱ አንፃር ከላይ የሚደረብ በተቋሙ የተዘጋጀ የተቋሙ አርማ፣ ስምና የሙያ መለያ ያለበት ሹራብ/ጃኬት መልበስ ይችላል።

2.1.11. ጤና ባለሙያው የግል ንፅህናውን በአግባቡ መጠበቅ ይኖርበታል።

2.1.12. ሁሉም  ሴት የነርስና ሚድዋይፍ ባለሙያ ነጭ የነርስ የራስ ቆብ ማድረግ አለባት።

## 2.2 ጌጣጌጥና መዋቢያ

2.2.1. ማንኛውም ጌጣጌጥና የሰውነት ንቅሳቶች በስራ ላይ ሲሆን መውለቅ ወይም መሸፈን አለባቸው።

2.2.2. መዋቢያዎች ፣ ሽቶዎች እና የላብ ማድረቂያዎች ታካሚንም ሆነ ሌሎች  የስራ ባልደረቦች የማይረብሹ መሆን አለባቸው።

2.2.3. በቀጥተኛ መልኩ ከታካሚ ጋር አካላዊ ንክኪ/direct body contact/ የሚኖራቸዉን ተግባራት የሚፈጽም የጤና ባለሙያ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የእጅ ሰዓት  ባይጠቀሙ ይመረጣል

2.2.4. በስራ ላይ ያለ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ጥፍር መጠቀም የማይችል ሲሆን ተፈጥሮአዊውም በአጭሩ የተቆረጠ ፣ የጥፍር ቀለም የሌለው እና ንፁህ መሆን ይኖርበታል።

2.2.5. የሴቶች ፀጉር በንፅህናና በአግባቡ የተያዘ ሆኖ ረጅም ፀጉር በስራ ወቅት ወደ ላይ በአግባቡ መያዝ ይገባዋል ወንዶችም በአጭር መቆረጥ ይኖርባቸዋል።

2.2.6. ወንድም ይሁን ሴት ባለሙያ ፀጉር አንጨባርሮ በስራ ገበታ መገኘት ፈፅሞ የተከለከለ ሲሆን የወንዶችም ፀጉር በአጭር መቆረጥ ይኖርበታል።

## 2.3 የግል ኤሌክትሮኒክስ መጠቀሚያ

2.31. ማንኛውም የግል የኤሌክትሮኒክስ መጠቀሚያ በስራ ሰዓት ለግል ጉዳይ መጠቀም አይቻልም።

2.32. አስገዳጅ የግል ሁኔታዎች ቢኖሩ ለቅርብ ሃላፊ በማሳወቅ ከስራ ቦታ ዉጭ ለምሳሌ ወደ ማረፊ ክፍል በመሄድ ለተፈቀደው ሰአት ልክ ተጠቅሞ መመለስ ይቻላል።

## 2.4 የተለያዩ የሥራ ክፍሎችና ሙያዎች የደንብ ልብስ አይነት እና ቀለም

2.4.1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በኦፕራሲዮን ክፍልና በፅኑ ህሙማን ክፍል በሚያገለግልበት ጊዜ ፈዛዛ አረንጓዴ (light green) ሙሉ የደንብ ልብሱን መልበስ አለበት፡፡

2.4.2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በድንገተኛ ክፍል በሚያገለግልበት ጊዜ በርገንዲ ቀለም (Burgendi) ያለው ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለበት፡፡

2.4.3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከላይ በስም ከተጠቀሱት ክፍሎች ውጭ በሚያገለግልበት ጊዜ

2.41.1 ሀኪሞች ብርማ (light silver) እና ሙሉ የደንብ ልብስ ነጭ ጋዋን መልበስ አለባቸው፡፡

2.41.2 ነርሶች ፈዛዛ ሰማያዊ (light blue ) ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለባቸው፡፡

2.41.3 ሚድዋይፎች ፈዛዛ ሀምራዊ (light purple) ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለባቸው፡፡

2.41.4 ሌሎች ባለሙያዎች(ላብራቶሪ፣ ፋርማሲ፣ ራድዮሎጂ፣ፊዝዮቴራፒ፣...ወዘተ) ጥቁር ሰማያዊ (dark blue) ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለባቸው

2.42 ማንኛውም የጤና ሳይንስ ተማሪ በጤና ተቋማት ውስጥ ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ በኮሌታው ዙሪያ ነጭ መለያ/ stripe/ ያለበት ሆኖ ሲመረቅ የሚኖረውን ሙያ ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለበት፡፡ ለምሳሌ የነርስ ሙያ ተማሪ የሚለብሰው የነርሶች ሙሉ የደንብ ልብስ ነው፡፡ የሚኖረው ነጭ መለያ/ stripe/ ብዛት እንደ ተማሪው የትምህርት ዘመን ይወሰናል፡፡ ማለትም አንደኛ አመት ተማሪ አንድ መለያ ሲኖረው እንደ ተማሪው የትምህርት ዘመን እየጨመረ ይሄዳል፡፡ የትምህርት ዘመን መለያው እጅጌው ጫፍ ላይ የሚደረገ ይሆናል፡፡

2.43 ማንኛውም የጤና ባለሙያ በህፃናት ክፍልና የስነ አእምሮ ህክምና ክፍል በሚያገለግልበት ጊዜ የደንብ ልብሱ የታካሚውን ስነ ልቦና ይረብሻል ተብሎ ከታመነበት ያለደንብ ልብስ አገልግሎቱን ሊሰጥ ይችላል፡፡

2.44 ይህ እንዳለ ሁኖ ጤና ተቋማት ጤና ባለሙያ ላልሆኑ የተቋሙ ሰራተኞች እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ መመሪያ በማይጣረስ መልኩ የራሳቸውን የአለባበስ ስርዓት መመሪያ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

## 2.5 የደንብ ልብስ ይዘት

2.51 የደንብ ልብሱ የጨርቅ አይነት አንደኛ ደረጃ ቴትራን 6000 መሆን አለበት፡፡

2.52 የደንብ ልብሱ የወገብ ማሰሪያ/መመጠኛ የገመድ ወይም ባለ ፕላስቲክ መሆን ይችላል፡፡

2.53 የደንብ ልብሱ የላይ አላባሽ በጎን በኩል መከፍት የሚችል መሆን አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3.1 የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት

የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ ስርዓት በሀገር አቀፍ በጤና ተቋም ደረጃ አለባበሳቸው ወጥ ለማድረግ እና ለመመሪያው ተፈጻሚነት የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት የሚከተለው ነው።

### 3.1.1. የጤና ሚኒስቴር ተግባር እና ሀላፊነት

1. የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ መመሪያ ማውጣት
2. በፌደራል ጤና ተቋማት መመሪያው እንዲተገበር ማድረግ
3. መመሪያዉ ለክልሎች ማስተዋወቅ
4. የመመሪያዉን ተፈጻሚነት ማገዝ ፣ መከታተል እና ማረጋገጥ፤
5. እንደ ሀገር ይህን መመሪያ መሰረት አድርገው የደንብ ልብስ ማቅርብ የሚችሉ ጋርመንቶች ይለያል እገዛ ያደርጋል።
6. መመሪያ ከመተላለፍ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ቅሬታዎች መፍትሄ መስጠት፤
7. መመሪያውን እንደ አስፈላጊነቱ መከለስ፣

### 3.1.2. የክልል ጤና ቢሮ ተግባር እና ሀላፊነት

1. በፌድራል ደረጃ የወጣውን የጤና ባለሙያዎች የአለባበስ መመሪያ ለክልሉ ጤና ተቋማት ማስተዋወቅ፤
2. የመመሪያዉን ተፈጻሚነት ማገዝ ፣ መከታተል እና ማረጋገጥ፤
3. መመሪያ ከመተላለፍ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ቅሬታዎች መፍትሄ መስጠት፤
4. እንደ ክልል ይህን መመሪያ መሰረት አድርገው የደንብ ልብስ ማቅርብ የሚችሉ ጋርመንቶች ይለያል እገዛ ያደርጋል።
5. በክልሉ የሰው ሀይል ልማት ላይ የአለባበስ ሥርዓት እንደ አንድ መስፈርት አድርጎ መውሰድ፤

6. በየአመቱ ለጤና ተቋማት ለደንብ ልብስ በቂ በጀት መመደብ ወይም እንዲመድቡ ማድረግ

### 3.1.3. የጤና ተቋማት ማኔጅመንት ተግባር እና ሀላፊነት

1. በየአመቱ በጤና ተቋማት ዉስጥ ለሚገኙት የጤና ባለሙያዎች የደንብ ልብስ በጀት መመደብ፤
2. የጤና ተቋማት በመመሪያው  መሰረት ሁለት የደንብ ልብስ በአንድ ዓመት መስጠት፤
3. የደንብ ልብስ በአግባቡ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት መቅረቡን ማረጋገጥ፤
4. የተሰጠዉ የደንብ ልብስ በአግባቡ መለበሱን በየጊዜዉ ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፡፡
5. ደንበኞች ጤና ባለሙያዎችን በቀላሉ መለየት እንዲችሉ የአለባበስ ስርዓቱን በተለያየ መንገድ ማስተዋወቅ
6. የጤና ባለሙያ ተማሪዎች ከመንግስትም ሆነ ከግል የትምህርት ተቋማት ወደ ሆስፒታሎች ለተግባር ልምምድ ሲመጡ ይህን መመሪያ እንዲተገብሩና በውል ስምምነታቸው(MOU) ውስጥ አካተው በመግባባት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማድረግ፤
7. በአከባቢው የአየር ንብረት አንፃር አሰፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ከላይ የሚደረብ በተቋሙ የተዘጋጀ የተቋሙ አርማ፣ ስምና የሙያ መለያ ያለበት ሹራብ/ጃኬት ለጤና ባለሙያው አዘጋጅቶ መስጠት፡፡

### 3.1.4. የጤና ባለሙያዎች አለባበስ ስርዓት ኮሚቴ መመስረት እና ተግባር እና ሀላፊነት

የጤና ባለሙያ የአለባበስ ስርዓት አስፈፃሚ ኮሚቴ ከተመላላሽ ህክምና ፣ከተኝቶ ህክምና፣ከድንገተኛ ህክምና፣የነርሲንግ ዳይሬክተር ወይም ሜትረን፣ከሰው ሀብት ልማት ክፍል፣ የሰራተኛ ተወካይ፤ ከግዢ ክፍል እና ከኳሊቲ ክፍል የተዋወጣጡ ባለሙያዎች ያቀፈ እና ብዛታቸው ከሰባት(7) ያላነሰ ይሆናል፡፡ ኮሚቴው በሜትረን እየተመራ የጥራት ክፍል እንደ ጸሀፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

1. ማንኛዉም የጤና ባለሙያ በስራ ላይ እያሉ የሚመለከታቸዉን የደንብ ልብስ መልበሳቸዉን ማረጋገጥ እና ድገተኛ ቁጥጥር በወር ሁለት ጊዜ ማድረግ
2. የደንብ ልብስ ጥራት፣ አይነት፣ መጠን መምረጥ፣ መከታተል እና ማረጋገጥ፤
3. ጥራት እና ደረጃውን ያልጠበቁ ግዢዎችን እንዲስተካከል ማድረግ፤

4. ከባለሙያዎች የሚነሱ ሃሳቦችና ቅሬታዎችን ማስተናገድ እና መፍትሄ መስጠት፤
5. የአለባበስ መመሪያውን ለባለሙያዎች ማስተዋወቅ፣ ማወያየት፣ ማስተማር እና ማጠናከር፤
6. የአለባበስ መመሪያ የተላለፈን ባለሙያ የቀረበበትን ክስ ማጣራት፣ መመርመር ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ፣በመመሪያው መሰረት ውሳኔ ማስተላለፍ፤

### 3.1.5. የባለሙያዎች እና ተማሪዎች ተግባር እና ሀላፊነት

1. በመመሪያው መሰረት የተቀመጡ የስነምግባር መርሆች ተከትለው የተሰጣቸዉን የደንብ ልብስ አሟልቶው የመልበስ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. የደንብ ልብሳቸውን ሳይለብስ ስራ ላይ መገኘት በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን መረዳት እና ከዚህ ባለፈ ለሚወስዱት መንኛውም እርምጃ ሃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዮ ልዮ ድንጋጌዎች

### 4.1 የመተባበር ግዴታ

1. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናባቸዋል ተብለው በመመሪያው የተዘረዘሩት አካላት በሙሉ ለመመሪያው ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆንበት ማንኛውም አካል በመመሪያው የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ተላልፉ የተገኘ እንደሆነ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 4.2. መመሪያው የሚሻሻልበት አግባብ

ይህ መመሪያ ነባራዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ መመሪያው ተፈጻሚ ከሚሆንባቸው አካላት በሚነሱ የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት መሻሻሉ በሕግ አውጭው አካል ሲታመንበት በማንኛውም ግዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 4.3 የተሻሩ እና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች እና አሰራሮች


ማንኛውም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን መመሪያ፣ የአሰራር ስርአት፣ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ የተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 4.4. መመሪያ ስለመተላለፍ

- አንድ ባለሙያ በወር ውስጥ ሁለት ጊዜ የአለባበስ ስርዓቱን ተከትሎ ሳይለብስ ቢቀር በአገልግሎት ክፍል ሓላፊ የምክር አገልግሎት እና የቃል ማስጠንቀቂያ በቅርብ ሓላፊው ይሰጠዋል፡፡ ለኮሚቴውም በግልባጭ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡
- አንድ ባለሙያ በወር ውስጥ ሶስት ጊዜ የአለባበስ ስርዓቱን ተከትሎ ሳይለብስ ቢቀር በቅርብ ሓላፊው የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ እንዲሁም ኮሚቴው በጹሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡
- አንድ ባለሙያ በወር ውስጥ አምስት ጊዜ የአለባበስ ስርዓቱን ተከትሎ ሳይለብስ ቢቀር አለባበሱን እንዲያስተካክል ከተደረገ በሐላ ስራውን እየሰራ ወደ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ይላካል፡፡ ለማስተካከል ፍቃደኛ ከልሆነ ግን ከስራ ክፍሉ ገብቶ እንዳይሰራ ታግዶ ወደ ሆስፒታሉ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ይላካል፡፡ ዲሲፕሊን ኮሚቴም የሲቭል ሰርቪስ ህግ ተከትሎ አሰፈላጊውን እርምጃ ይወስድበታል፡፡
- አንድ ባለሙያ የአለባበስ ስርዓቱን ተከትሎ ሳይለብስ ቢቀር እና ከዛ በፊት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የቃል እና የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከነበረ በኮሚቴው ወደ ህክምና ክፍል ገብቶ እንዳይሰራ ታግዶ ወደ ሆስፒታሉ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ይላካል፡፡ ዲሲፕሊን ኮሚቴም የሲቭል ሰርቪስ ህግ ተከትሎ አሰፈላጊውን እርምጃ ይወስድበታል፡፡

## 4.5. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

መመሪያው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ የፀና ይሆናል፡፡


ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

ስም አሚር አማን (ዶ/ር) ሚኒስትር

ፊርማ

ቀን 20/01/12

# 4.6 አባሪ

## የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የደንብ ልብስ አይነት እና ቀለም

1.ማንኛውም የጤና ባለሙያ በኦፕራሲዮን ክፍልና በፅኑ ህሙማን ክፍል በሚያገለግልበት ጊዜ ፈዛዛ አረንዴ (light green) ሙሉ የደንብ ልብሱን መልበስ አለበት፡፡




3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በድንገተኛ ክፍል በሚያገለግልበት ጊዜ በርገንዲ ቀለም (Burgendi) ያለው ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለበት፡፡





4. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከላይ በስም ከተጠቀሱት ክፍሎች ውጭ በሚያገለግልበት ጊዜ

1. ሀኪም **እርሳስ ከለር** (light silver) እና ነጭ ጋዋን መልበስ አለበት፡



2. ማንኛውም ሚድዋይፍስ ባለሙያ ፈዛዛ ሀምራዊ (light purple) ሙሉ የደንብ ልብሱን መልበስ አለበት፡፡



5. ማንኛውም ነርስ ባለሙያ ሙሉ ፈዛዛ ሰማያዊ (Light Blue) የደንብ ልብስ መልበስ አለበት




6. ከላይ ከተጠቀሰው የስራ ክፍልና ሙያ ዉጪ የሆኑ ሁሉም ባለሙያዎች (ላብራቶሪ፣ ፋርማሲ፣ ራድዮሎጂ፣ፊዝዮቴራፒ፣...ወዘተ) ሙሉ የደንብ ልብስ **ጥቁር ሰማያዊ ( blue black )**




7. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በህፃናት ክፍልና የስነ አእምሮ ህክምና ክፍል በሚያገለግልበት ጊዜ የደንብ ልብሱ የታካሚውን ስነ ልቦና ይረብሻል ተብሎ ከታመነበት ያለደንብ ልብስ አገልግሎቱን ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. ማንኛውም የጤና ሳይንስ ተማሪ በጤና ተቋማት ውስጥ ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ በኮሌታው ዙሪያ ነጭ መስያ /stripe/ ያለበት ሆኖ ሲመረቅ የሚኖረውን ሙያ ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ አለበት ፡፡ እንዲሁም በእጀጌው ጫፍ የትምህርት ዘመን የሚገልፅ ነጭ መስያ/ stripe /የሚኖረው ሲሆን ነጭ መስያ (stripe) ብዛት እንደ ተማሪው የትምህርት ዘመን ይወሰናል ማለትም አንደኛ አመት ተማሪ አንድ መስያ ሲኖረው እንደ ተማሪው የትምህርት ዘመን መስያው እየጨመረ ይሄዳል፡፤ የትምህርት ዘመን መስያው የእጀጌው ጫፍ ላይ የሚደረግ ይሆናል፡፡

9. **ከላይ የተመረጡ የልብስ ቀለማት 3 ነገሮችን ከግምት በማስገባት ነው**

1. ቀለሞቹ በጤና ባለሙያውና በተገልጋዮ ማህበረሰብ(በታካሚው) ባጠቃላይ በአገልግሎቱ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊና አዎንታዊ ስሜት በሳይንሳዊ ጥናት ምን እንደሆነ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰማያዊ ቀለም ለእይታ የማይከብድና ተስፋን የሚጭር ብለው የቀለም ባለሙያዎች ይገልፁታል እንዲሁም አረንጓዴ ቀለም የደም(የቀይ ቀለም ተቃርኖን ባላንስ የማድረግ አቅም አለው ተብሎ ይታመናል ለዚህም ነው አረንጋዴ ቀለም ለቀዶ ህክምናና ለፅኑ ሁሙማን ክፍል ባለሙያዎች እንዲሆን የተደረገው እንዲሁም በርገንዲ ቀለም sense of urgency, I am stand by and ready የሚል መልዕክት/ትርጉም አለው ተብሎ ይገለፃል በመሆኑም ለድንገተኛ ክፍል ተመራጭ ቀለም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
2. የባለሙያዎች እይታና ምርጫ (Professional Perspective) መሰረት ያደረገ ነው ማለትም ከተለያዩ ጤና ተቋማት እና የሙያ ማህበራት የመጡ ባለሙያዎች ባዘጋጀናቸው የተለያዩ መድረኮች የሰጡት አስተያየት መሰረት ያደረገ ነው፡፡
3. አለም አቀፍ ልምዶች ምን ይመስላሉ የሚለውንም በተጨማሪ መሰረት አድርጓል፡፡ የተለያዩ ሀገራት ጤና ተቋማት እንዲሁም በአገር ውስጥ ያሉ የግልና የመንግስት ሆስፒታሎች ያላቸው የአለባበስ ስርዓት ከግምት በማስገባት ጭምር ነው እዚህ ድምዳሜ የተደረሰው፡፡

10.የደንብ ልብስ የአሰፋፍ ዲዛይን በሁለቱም አመራጭ ሊሰፋ ይችላል






10. የጫማ ዓይነትና ዲዛይን



**Figure 1 General shoes**




Figure 2 OR shoe





